**የኢትዮጵያ፤የውይይትና መፍትሔ መድረክ (ኢውመመ) 9900 Greenbelt RD. E#343 - Lanham,**

**MD 20706 – Tel: 1-202-641-5517**

# <u>የወቅቱን የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚመለከት ከኢትዮጵያ ውይይትና መፍትሄ መድረክ (EDF) የወጣ መግለጫ</u>

የሃገራችን ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ከመቼውም ጊዜ በላይ አሳሳቢ ሆኗል። ኢትዮጵያውያን በተለይ ላለፉት ሶስት ዓመታት በተከታታይና በመረረ ሁኔታ መንግስታቸውን ሲቃወሙ ይታያል። እንዲህ ያለ በተከታታይና በቆራጥነት የተካሄደ ሕዝባዊ ተቃውሞ በሃገራችን ታሪክ አልታየም። ገበሬዎች ሰልፍ ወጥተው “የህወሓት አገዛዝ በቃን” እያሉ ነው። የትናንሽ ከተማ ነዋሪዎች በነቂስ እየወጡ በመረረ ሁኔታ ሲጮሁ ይሄው ሶስት ዓመት ሆነ። ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እየወጡ ለውጥ እንፈልጋለን ሲሉ ይታያል። ነጋዴው ሱቁን እየዘጋ ተቃውሞውን ያሰማል። ኢትዮጵያውያን ያለ ልክ ለውጥ የፈለጉ መሆናቸውን የሚያሳይ መራራ ተቃውሞ በሃገሪቱ በሰፊው በየቀኑ ይታያል። ይሁን እንጂ ተቃውሞ በሚነሳባቸው አካባቢዎች የመንግስት ታማኝ ወታደሮች፤ በተለይ አጋዚ፤ የፌደራል ፖሊስና ልዩ ታጣቂዎች፤ ደህንነት በሚወስዱት ግብታዊ ርምጃ በየሰልፉ ላይ የንጹሃን ህጻናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን ደም ይፈሳል። መንግስት ተቃውሞ በሚነሳባቸው አካባቢዎች ሁሉ ወታደር እየጫነ እየወሰደ ዝም ሊያሰኝ ቢሞክርም ተቃውሞው እየበረታ መጥቷል። መንግስት በሚወስደው ርምጃ በነዚህ ሶስት ዓመታት ውስጥ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል። ከአስራ አንድ ሽህ በላይ ታስረዋል፤ ሌሎች እንዲሰወሩ ተደርጓል። ባለፈው ጊዜ በኦሮምያ ክልል በኢሬቻ በዓል ቀን ብቻ ወደ ሰባት መቶ ሰዎች እንደሞቱ ይታወቃል። በአማራው ክልል የተገደሉት ወገኖቻችን ቁጥር በቅጡ ባይታወቅም፤ ብዙ መቶዎች እንደተጨፈጨፉ ተነግሯል። በቅርቡ በጨለንቆ አካባቢ ብዙ ሰላማዊ ሰዎች እንደተገደሉ ዜናዎች ተሰምተዋል። በአዲግራት የሚማሩ የአማራ፤ የኦሮሞና ሌሎች የትግራይ ብሄር አባል ያልሆኑ ተማሪዎች ተገድለዋል።

ባላፈው ሶስት ዓመት ውስጥ ባለው ተከታታይ ተቃውሞ በተለይ በገጠሩ አካባቢ ከሚገመተው በላይ ሰው እንደሚሞት እንገምታለን። ሃገሪቱ በመረጃ መረብ የዳበረ ግንኙነት ስለሌላት፣ ጋዜጠኞች ግጭት ወዳለበት አካባቢ እንዳይሄዱ ስለሚከለከልና ብዙ የሲቪክ ድርጅቶች ስለተዘጉ መረጃዎች አይወጡም እንጂ በየቀኑ የሚሞተው ሰው ከሚገመተው  በለይ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ሃገራችን ኢትዮጵያ ከገጠማት አሳሳቢ ነገር አንዱ ደግሞ የወቅቱን የብሄርና የጎሳ ፖለቲካ ተከትሎ በመጣው የመተማመን መውረድ ጋር ተያይዞ የብሄር ግጭቶች በሰፊው ይታያሉ። ህዝቡ በአንድ በኩል ከመንግስት ጋር እየታገለ በሌላ በኩል ስርዓቱ ያፈራቸው ጽንፈኛ ብሄርተኞች ደግሞ ሌላ የሃገር ህልውና ስጋት ሆነውበታል። በቅርቡ በኦጋዴን አካባቢ ብቻ ከሰማንያ  ሺህ በላይ የሚገመቱ የኦሮሞ ብሄር አባላት ከሶማሊያ ክልል ተፈናቅለው ዓለም ደንግጧል። ይህ ብቻ ሳይሆን

የትምህርት ሚንስቴር በቅርቡ ከሱማሌ ክልል ተወላጅ ውጭ የሆኑትን የሌላ ብሄር ተወላጆች ሶማሊያ ክልል በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች እንዳይማሩ መደረጉ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ግራ ያጋባ፣ ያሳሰበ ነገር ነበር። ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያውያን በነጻነት በአሜሪካ፣ በብሪታኒያ፣ በኖርወይ፣ በአውስትሬሊያ፣ በካናዳ፣ በስዊድን፣ በጀርመንና በሌሎች አገሮች ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች እየተማሩ በሃገራቸው ምድር በብሄራቸው ብቻ በነጻነት መማር ያለመቻላቸው የብሄር ግጭት በኢትዮጵያ የደረሰበትን ደረጃ ያሳያል። በርግጥ ይህ ዜና ለብዙ ኢትዮጵያውያን አሳፋሪ ነው።

ባለፉት ጥቂት ቀናት ደግሞ ሃገሪቱ ተስፋ ከምትጥልበት የትምህርት ተቋም ውስጥ የብሄር የጎሳ ግጭት እየታየ መምጣቱ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ሆኗል። አስራ ሁለት በሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ተቃውሞዎች እየተሰሙ ሲሆን በአንዳንድ የትግራይ፣ የአማራና የኦሮሞ ዩኒቨርሲቲዎች ብሄር ተኮር ግጭቶች ታይተዋል። ይህ ግጭት የሊጋ ተማሪዎችን ህይወት ቀጭቷል። የብሄር ተኮር ግጭቱ በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢ መታየቱ ነው የበለጠ አሳሳቢ ያደረገው።

በተለይ ባለፉት ሶስተ ዓመታት ካለው ሰፊ ህዝባዊ ተቃውሞ የተነሳ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ክፉኛ ተጎድቷል። የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ረሃብ በሰፊው ይታያል። ስደትና መፈናቀል በየቤቱ ገብቷል። ወጣቶች ሃገር ጥለው ይጠፋሉ። በየመንና በሊቢያ ለባርነት እየተሸጡ ነው። የሃገር ውስጥ መፈናቀሉ ቀጥሏል። ይሁን እንጂ ሃገሪቱ በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ወድቃ፣ መንግስት በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ተዘፍቆ፣ ለዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብም ሆነ ለኢትዮጵያውያን ችግሩን ማንሳትና መሰረታዊ ችግሮችን ለመፍታት ኣይፈልግም። ይህ የመረረው ህዝብ አንድ ቀን ጮሆ ጮሆ ሲበቃው ዝም ይላል ብሎ ይጠብቅ እንደሆነ አናውቅም። መንግስት ዘላቂ የሆነ ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት ሲሰራ አይታይም። አገር ቤትና ከሃገር ውጭ ካሉ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ውይይትና ድርድር ለማድረግ አልፈለገም። ይህ ሁሉ መራራ ተቃውሞ እያለ፣ የዚህ ሁሉ ህዝብ እንባ ሲፈስ እያየ ገዢው መንግስት ልቡ ሲሰበር ኣናይም። መንግስት ይህ ሁሉ ችግር እያለበት "በተሃድሶ ጎዳና" ላይ ነን ይላል። ይህ የመንግስት ዝንባሌ እጅግ አሳሳቢ ሆኖ እናያለን።

የኢትዮጵያ የውይይትና መፍትሄ መድረክ የሃገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አሳብ ላይ ስለጣለን የሚከተለውን መልእክት ለሚመለከታቸው ሁሉ ማስተላለፍ እንሻለን።

## <u>*ሀ. ለኢትዮጵያውያን ያለን ጥሪ*</u>

1. ኢትዮጵያ ውስጥ የለውጥ ባቡር በጉዞ ላይ ነው። ኢትዮጵያውያን ሽግግር ፈልገዋል። ግፍ፣ ዘረኝነትና፣ አምባገነን ስርዓት አንገሽግሿቸዋል። የህዝቡ ጥያቄ በሃገሩ ህግም ይሁን በዓለም ዓቀፍ ህጎች ተቀባይነት ያለው ነው። ስለሆነም ህዝቡ ትግሉን በሰላማዊ መንገድ እንዲገልጽ እያበረታታን፤ ነገር ግን በትግሉ ወቅት ብሄር ተኮር ግጭቶች ሲነሱ ጽንፈኞችን መታገል ይኖርበታል። ያለመታደል ሆኖ ትግሉ አምባገነን ስርዓትን ለመጣል ብቻ ሳይሆን የብሄር ፖለቲካው ያፈራቸው ጽንፈኞችም ህዝባዊ ኣመጾችን ተገን እያደረጉ የብሄር ግጭት ስለሚያነሱ ይህንን ህዝቡ ነቅቶ እንዲጠብቅ እንመክራለን።
2. በየትኛውም የስልጣን ርከን ላይ ያላችሁ የመንግስት ባለስልጣናት የዚህ ህዝብ እንባ ግድ ሊላችሁ ይገባል። በመሆኑም በየመስሪያ ቤታችሁ ህዝቡ ድምጹ ይሰማ ዘንድ ጥያቄዎችን እንድታነሱ፣ ከህዝብ ጥያቄ ጎን እንድትቆሙ ያስፈልጋል። ይህ ወቅት ታሪካዊ ወቅት ነውና በዚህ ታሪካዊ ወቅት ከህዝቡ ጎን ቆማችሁ ሃገራችሁን እንድትታደጉ እንጠይቃለን። በተለይ በወታደሩና በጸጥታው ክፍል ውስጥ ያላችሁ ወገኖች መንግስት የህዝቡን ጥያቄ ለማፈን የሚጠቀምበት ዋና መሳሪያ በመሆናችሁ በዚህ ወቅት ከህዝብ ጎን ትቆሙ ዘንድ እንጠይቃለን።
3. በሃገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ያላችሁ ተማሪዎች፤ ትግላችሁን እናደንቃለን፤ ሳይማር ያስተማራችሁን አባታችሁን፣ ሳትማር ያስተማረቻችሁን እናታችሁን፣ ተስፋ የሚያደርጋችሁን ገበሬ አስቡ። ሃገራችን ይህን ተቋም ነው ተስፋ የምታደርገው። የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመቅረፍ፣ ዘረኝነትንና ኣድልዎን ኣጥፍቶ ፍትህን ለማምጣት፣ ከድሃነት ወጥተን ለራሳችን የምንበቃ እንድንሆን ሃዋርያት ትሆናላችሁ ተብላችሁ የምትጠበቁ ብርቅየ ልጆች ናችሁ። ታዲያ በዚህ ተስፋ ከተጣለበት ተቋም ውስጥ የብሄር ግጭት የሚያስነሱ ጽንፈኞች ሲነሱ ልትዋጉት ይገባል። የሚያጋጫችሁ ሃይል የኢትዮጵያን የሽግግር ወቅት ለማበላሸት፣ የኢትዮጵያውያንን የለውጥ ጥያቄ ለማበላሸት ነውና ይህንን ጸንታችሁ ታገሉ። በአንድነት ተነስታችሁ የህዝቡን የለውጥ ጥያቄ አስተጋቡ።
4. የተለያዩ የሲቪክ ማህበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች ከመቼውም ጊዜ በላይ በህብረት የኢትዮጵያውያንን የለውጥ እንቅስቃሴ መደገፍ ያስፈልጋል። የብሄር ግጭት ሲታይ ጽንፈኝነት ሲታይ ይህንን በማውገዝ ቀዳሚ ትሆኑ ዘንድ እንጠይቃለን።
5. የሃይማኖት ተቋማት በኢትዮጵያ የለውጥ ትግል ውስጥ ልትሳተፉ ይገባል። በማስታረቅ፣ የለውጥ ጥያቄውን በመደገፍና በጸሎት የኢትዮጵያውያንን የለውጥ ትግል እንድትደግፉ በአክብሮት ጥሪ እናደርጋለን።

**ለ. ለዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ያለን ጥሪ**

1. ኢትዮጵያ ባሳለፈቻቸው የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ከጎን በመሆን፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል በመደገፍ መግለጫ ስታወጡ ህማማችንን ስትካፈሉ ለነበራችሁ ዲፕሎማቶች፣ የዓለም ዓቀፍ ተቋማትና ልዑካን ሁሉ ምስጋናችን ብዙ አድናቆታችንም እጥፍ ድርብ ነው። በግልጽ ከምታደርጉት በጋዜጣ ከምናነበው ውጭ የኢትዮጵያን መንግስትን በመምከር አቅጣጫ በማሳየት እንደምትደክሙ ይሰማናል። ይሁን እንጂ መንግስት የሚሰጠውን ምክር ችላ እያለ፣ የሚሰጣቸውን የለውጥ ተስፋዎች እያዘገየ፣ እያስረሳና እያዘናጋ ጊዜ መፍጀት ብቻ ነው የሚፈልገው። ለእውነተኛና ሁሉን አቀፍ ምክክር ልቡን አይሰጥም። በመሆኑም እንደምታዩት ዛሬ በየዩኒቨርሲቲው የብሄር ተኮር ግጭት ሳይቀር መታየት ጀምሯል። ሩዋንዳ ውስጥ አንድ ትምህርት ቤት የተነሳ ግጭት ሃገሪቱን በጥቂት ጊዜ አዳርሶ ዓለም የዘገነናትን ወንጀል አይተናል። በአሁኑ ሰዓት የዘር ፍጅት ተግባራት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢ እየታየ በመሆኑ ይህ ጉዳይ የሚያሳስባችሁ እንደሆነ እናውቃለን። በመሆኑም ከፍተኛውን ተግባራዊ ርምጃ በመውሰድ ይህን መንግስት ወደ ድርድር እንዲመጣ ተጽእኖ እንድትፈጥሩ በትህትና እንጠይቃለን።

2. እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ለዓለም ስጋት ከሆነው የሽብር ጥቃት በተለይም ለአልሸባብ እንቅስቃሴ የተጋለጠች አገር ናት። ይህን ሃይል ለማዳከም ብሎም ቀጣናውን ከሽብር ስጋት ነጻ ለማድረግ ኢትዮጵያ ትልቅ ሃላፊነት ትከሻዋ ላይ አለ። ፔንታጎን በዚህ ቀጣና ያለውን አሸባሪ ለማጥፋት የሚያደርገውን ንቅናቄ እያደነቅን ኢትዮጵያ በዚህ ቀጣና ሽብር የመከላከል አቅሟ ከፍ ይል ዘንድ የውስጥ መረጋጋትና ሁሉን አቀፍና ዲሞክራሳዊ መንግሥት ያስፈልጋታል። የኢትዮጵያ የውስጥ አለመረጋጋት በአንድም በሌላም መንገድ ለሽብር እንቅስቃሴ መጋቢ ችግር ስለሚፈጥርና በቀጣናው ሰላም ላይ አሉታዊ ጫና ስለሚኖረው በአንድም በሌላም መንገድ ፔንታጎን ከኢትዮጵያውያን የለውጥ ፍላጎትና ጥያቄ ጋር እንዲቆምልን በአክብሮት እንጠይቃለን።
በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰላም ኣስከባሪ ክፍሉም በኢትዮጵያ ውስጥ መረጋጋትን ያላመጣ መንግስት ጸረሽብር ስራ ሊሰራ ስለማይችል ሁኔታውን ተረድቶ በግንኙነት መስመሮቹ ሁሉ ለውጥ በኢትዮጵያ እንዲመጣ እንዲታገልልን እንጠይቃለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ይጠናከር!!

ታህሳስ 7 ቀን 2010 ዓ.ም